# ቅቤውና ሱሴ

ዛሬም አልነጋልሽ ፣ እማማ ሃገሬ
ነግሶልሻል አሉ ፣ ሰው የመሰለ አውሬ

በጣቃው መተርተር ፣ ችሎታና አመሉ
ሰማይና ምድር ፣ ስራውና ቃሉ ።

አግኝተን አናውቅም ፣ እንዲህ ያለ መሪ
ቤት እያፈረሰ ፣ መናፈሻ ሰሪ ።

ያቀፈ አስመስሎ ፣ የሚናከስ ጀግና
ተክኖታል መቼም ፣ ማታለል በቁና ።

በመድረክ ችሎታው ፣ እየተሸሸገ
የደሃውን እንባ ፣ መስሎ የጠረገ
    አጦራት ኢትዮጵያን ፣ ዛሬ እንደፈለገ
    የታመነበትን ፣ ተስፋ አጠወለገ ።

ባሉት ተቃራኒ ፣ እየተገበሩ
የሚሰራው ስራ ፣ ምን ይሆን ሚስጥሩ
        ምላሳቸው ታስሯል ፣ እንግዲህ ፓስተሩ
        ሰባተኛው ንጉስ ፣ መቼ ተናገሩ ።

ውሃ አልቋጥር ብሏል ፣ እመኑኝ ማለቱ
እውነት ቀኗን ቆርጣ ፣ ቆማለች ከፊቱ ።

በዛሬው አያያዝ ፣ እንዳካሄዳቸው
ልክ እንደ ወያኔ ፣ ሃያ ቢሞላቸው
        በነሱ አረማመድ ፣ በነሱ መወጠር
        እንኳንስ ፣ የሰው ዘር ፣ ወፍ አይኖርም ባገር ።

ሁለተኛው ንጉስ ፣ ሌላኛው ምስለኔ
ምንድነው ተግባሩ ፣ አልገባኝም እኔ ።

አልጋ ወራሽ ይሁን ፣ ወይ ንጉስ ፣ እራሱ
ድንገት የሰማነው ፣ ኢትዮጵያዩ ሱሱ
    እንዳንጠረጥረው ፣ ከትቦን በስሱ
    ለካስ ኬኛ ፣ ኬኛ ፣ ነበረ ድግሱ ።

እነ ዳላስ ቀርተው ፣ ሚቺጋን አትላንታ
ቆንስላ ከፈተ ፣ ሱሴም ሚኒሶታ
የዘፈን ዳር ዳሩ ፣ ሚስጥሩ ሲፈታ
እያመቻቹን ነው ፣ ለጫጫሩት ካርታ
    ቆንስላው ሲከፈት ፣ የሰማነው መዝሙር
    የኢትዮጵያ አይደለም ፣ አገር ነን በጃዙር ።

በምኞት ያበዱት ፣ የዘውጌ ምርኮኛ
እነ ሁሉ አማረሽ ፣ አዲሳባ ኬኛ
ታሪኩም ፣ አገሩም ፣ ሁሉም ፣ የኛ የኛ
የሁሉ አዋቂዎች ፣ አይፈልጉ ዳኛ
    ሌላ ቃል የለውም ፣ የነሱ ኦሮምኛ
    ቅቤውና ሱሴ ፣ ሸወዱን ክፉኛ ።

ታዛቢው

March 5, 2019